**GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA**
**EXECUTIVE OFFICE OF THE MAYOR**

Keeping DC Schools Safe for All (Amharic)

# ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን፣ ለሁሉም የሠላም ዋስትና የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ማድረግ (Keeping DC Schools Safe for All)

**ልብ ይበሉ፣ ፤**

- **ተማሪዎች ሁሉ ለሕዝብ ትምህርት ሕጋዊ መብቶች አሏቸው።** ልጆችንና ወላጆችን፣ የኢሚግሬሽን ወይንም የዜግነት ጉዳያቸው የፈለገውን ዐይነት ቢሆንም፣ ዲሲፒኤስ እና ዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፣ ልጆችን እና ወላጆችን በደስታ ይቀበላሉ። ልጆቻችን ከትምህርት ቤት ሲውሉ፣ ትምህርቶቻቸውን ሲማሩ እና ለወደፊት ኑሮአቸው ሲዘጋጁ፣ ከተማችን የደህንነት ዋስትና የሰፈነባት ጠንካራ እንደምትሆን እናውቃለን። ትምህርት ቤቶቻችንን ለሁሉም ክፍት እንዲሆኑ ማድረግ የዲሲ እሴት ብቻ ሳይሆን፣ በሀገሪቱ ጠቅላይ የህግ መወሰኛ ፍርድ ቤት ጉዳይ -(Suprem Court) – *Plyler v. Doe* – የተጠበቀ ሲሆን ተማሪዎች ሁሉ የኢሚግሬሽን ሁኔታቸው ሁሉ የፈለገውን ቢሆንም የሕዝብ ትምህርት የማግኘት መብታቸው በሕግ የተከበረ ነው።

- **የዜግነትዎን እና የኢሚግሬሽን መረጃዎን – እንዲሁም የልጅዎን መረጃ አይጠየቁም ወይንም ሌሎች እንዲያውቁት አይደረግም።** የትምህርት ቤት ባለሥልጣናት፣ ወላጆችን፣ ስለዜግነታቸውም ሆነ ስለ ኢሚግሬሽን ሁኔታቸው መረጃዎች እንዲሰጡ አይጠይቁም። የአንድን ቤተሰብ የኢሚግሬሽን ጉዳይ መረጃ ለትምህርት ቤት ባለሥልጣናት በሚገለጽበት ጊዜ፣ ዲሲፒኤስ እነዚህን መሰል መረጃዎች፣ የተማሪው የትምህርት መረጃ ማስረጃዎች በተቀመጡበት ማኅደር ውስጥ እንዲቀመጥ መዝግቦ አይዝም። ከዚህም ባሻገር፣ የፌድራላዊው እና የዲስትሪክት የግል መብት ማስከበሪያ ሕጎች፣ የወላጅ ስምምነት የገኀደለውን የተማሪዎች የትምህርት ማስረጃዎች ይፋ ከመውጣት ይከላከላል። እነዚህን መረጃዎች፣ እስከሚቻለው ሁሉ ዲሲፒኤስ በምሥጢር ተጠብቀው እንዲያዙ ያደርጋል። የተማሪዎችን እና የወላጆችን የግል መረጃዎች ይፋ ማድረግ፣ ተማሪዎች ሁሉ የሠላም ዋስትና እንዲሰማቸው እና የሁላችንም አካል ሆነው እንዲካተቱ ለማድረግ በቁርጠኛነት የቆምንለትን ዐላማ እና መንፈስ ይጻረራል።

- **የግንኙነት መረጃዎች ወቅቱን የጠብቁ ሆነው እንዲገኙ ያድርጉ።** አሁን ከምን ጊዜውም የበለጠ፣ የልጅዎ የአስቸኳይ ድንገተኛ ጊዜ መረጃ ቅጾች ተሟልተው የሚገኙ እና ትክክልነት ያላቸው ሆነው እንዲገኙ ያድርጉ። እንደ ወላጅነትዎ ወይንም አሳዳጊነትዎ ድንገት ቢታሰሩ፣ ልጅዎን ሰብስቦ የሚይዙልዎ ሰዎችን የመገናኛ መረጃዎችን ያካትቱ። ከቤትዎም ልጆችዎ እነዚህን የመገናኛ ቁጥሮች በቃላቸው እንዲዙ ያድርጉ። ልብ ይበሉ፣ የትምህርት ቤት የአስቸኳይ ድንገተኛ ጊዜ ቅጾች መረጃዎች፣ እንዲህ ዐይነቱን መረጃ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ በህግ የተረጋገጠ እስካልሆነ ድረስ፣ ለፌድራል ባለሥልጣናት ይፋ አይደረጉም።

  **የመጠባበቂያ እቅድ ለማዘጋጀት አስቡ።** ምንም እንኳን የሆነ አንዳች ችግር ሊኖር አይችልም ብለን ተስፋ ብናደርግም፣ ቀደም ብሎ ዝግጅት ማድረግ ይጠቅማል እንጂ ከቶ አጎዳም። የሚጨነቁ ከሆነ መጠባበቂያ እቅድ ያዘጋጁ። እስር ወይንም ከአገር መባረር ካጋጠምዎ–ልጆች እንዲጠበቁልዎ አንድ ሰው፣ ዘመድ ወይንም ጓደኛ ስለ ማዘጋጀት ጉዳይ የኢሚግሬሽን መብቶችን ወይንም የህግ ድርጅቶችን ያነጋግሩ። ልጆችዎ እዚህ ዩናይትድ ስቴትስ እንዲቀሩ፣ ወይንም ከእርስዎ ጋር እንዲመለሱ ይፈልጉ እንደህነ ይወያዩ።

- **የጠርፍ ጥበቃ እና የግምሩክ ቀረጥ መሥሪያ ቤት (ICE) ወደ ትምህርት ቤት ዘልቆ የመግባቱ ሁኔታ በጣም የመነመነ እድል ነው ያለው።** በአሁን ጊዜ በሚሠራበት በፌድራሉ ህግ ፖሊሳ መሠረት፣ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ ለእስር የሚያዙበት፣ የምርመራ ቃል የሚሰጡባቸው፣ የሚፈተሹበት፣ ወይንም ደፈጣ የሚካሄድባቸው ቦታዎች እንዳልሆኑ፣ የጠርፍ ጥበቃ እና የጉምሩክ ቀረጥ መሥሪያ ቤት (ICE)፣ ትምህርት ቤቶችን "ጥንቃቄ የሚደረግባቸው ቦታዎች" ("sensitive areas") እንደሆኑ አድርጎ ይመለከታቸዋል። የጠርፍ ጥበቃ እና የጉምሩክ ቀረጥ መሥሪያ ቤት (ICE)፣ እነዚህ ሁኔታዎች በትምህርት ቤት እንዲካሄዱ የሚፈቀደው፣ ሞት ሊደርስ ይችላል፣ ሁከት ይፈጠራል፣ ወይንም አካላዊ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ብሎ በሚገመትበት ጊዜ ብቻ ነው።

**መብቶችዎን ምን ጊዜም አይዘንጉ።**

- **ተማሪዎች ሁሉ፣ የህጋዊ ነዋሪነት ደረጃ ኖራቸው አልኖራቸውም ፣ ለጽሙማንንነት (disability) እና በሌሎችም ምክንያት ለሚገኙ ጥቅማ ጥቅሞች ተጠቃሚ የመሆን መብቶች እንዳሏቸው ያስተውሉ።** ተማሪዎች ሁሉ የትምህርት ቤት ምሳዎች፣ ቁርሶች፣ ለሌሎችም የልዩ ትምህራዊ አገልግሎቶች የነዋሪነት ህጋዊ ወረቀቶች ኖራቸው አልኖራቸውም፣ የተጠቀሱትን አገልግሎቶች የማግኘት መብቶች አሏቸው። አንድ ጊዜ አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እግሩ ከረገጠ፣ ነዋሪ መሆን ባለመሆን ምክንያት ህጉ አንዳችም ዐይነት መድልዎ አያደርግበትም።

- **ችሎት በሚካሄዱባቸው በመንግሥታዊ አገልግሎቶች፣ በሚገባዎት ቋንቋ የመጠቀም መብትዎ የተከበረ ነው።** ህጋዊ የነዋሪነት ደረጃዎ የተጠበቀ ሆነ አልሆነም፣ በመንግሥታዊ ችሎቶች በሚገባዎት ቋንቋ የመጠቀም መብት አለዎት። በማናቸውም መንግሥታዊ ወኪል ድርጅቶች፣ የወላጅ መምህር ስብሰባዎች ወይንም በተማሪዎ ግላዊ ትምህርታዊ እቅድ፣ ስብሰባዎችን ጨምሮ አስተርጓሚም ሆነ የተተረጎመ ጽሁፍ ካስፈለግዎ እነዚህን አገልግሎቶች ለመጠየቅ አያመንቱ። ትርጉሞች እና ተርጓሚዎች ማግኘት መብትዎችዎ ሲሆኑ፣ እነዚህም መብቶች በዲስትሪክቱ ፖሊስ ጣቢያም ይሁን ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡባቸው ጊዜያት ብቻ ሳይሆን፣ ከጠርፍ ጥበቃ እና የጉምሩክ ቀረጥ መሥሪያ ቤት (ICE)፣ ወይንም ከፌድራላዊው የኢሚግሬሽን ባለሥልጣናት ጋር ንግግር በሚኖርዎት ጊዜ እነዚህ መብቶችዎ የተጠበቁ እና የተከበሩ ናቸው።

- **ከፌድራላዊው የኢሚግሬሽንም ሆነ ከጠረፍ ጥበቃ እና የጉምሩክ ቀረጥ መሥሪያ ቤት (ICE) ባለሥልጣናት ጋር የመነጋገር መብቶችዎን ልብ ይበሉ።** ከታሪክ ወይንም በፌድራላዊው የኢሚግሬሽን እና/ወይንም በጠርፍ ጥበቃ እና የጉምሩክ ቀረጥ መሥሪያ ቤት (ICE)፣ ባለሥልጣን ዘንድ የሚቀርቡ ከሆነ፣ ከመቅረብዎ በፊት በዲሲ የህግ አገልግሎቶች (Immigrant Justice Legal Services (IJLS)) የበጎ አድራጎት ችሮታ በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም በሚካሄድ ድጎማ መብቶችዎን የማወቂያ ሥልጠና ላይ ለመሳተፍ አስቡ። ሥልጠናም ይሁን ወይንም ድርጅት ለማግኘት እርዳታ ካስፈለገዎ የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣናትን ይጠይቁ ወይንም በስደተኞች የህግ እና የፍትህ አገልግሎቶች (IJLS) ችሮታ የሚሰጣቸው፣ በከንቲባዋ የአፍሪካ ጉዳዮች ድርጅት ጽሕፈት ቤት ድረ ገጽ (Mayor’s Office of African Affairs website)፣ ተዘርዝረው የቀረቡትን፣ የከንቲባዋ የላቲኖች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት , (Mayor’s Office of Latino Affairs website) ድረ ገጽ እና የከንቲባዋ ጽህፈት ቤት፣ ኤሽያን የፓሲፊክ ደሴት ድረ ገጽ (Mayor’s Office of Asian and Pacific Islanders website) ላይ የሚሰፍሩትን ዝርዝሮችን ይጠይቁ ወይንም ይመልከቱ።

**በከተማ አገልግሎቶች ያለ ሥጋት እና ፍራቻ መገልገልዎን ይቀጥሉ።**

- **የሜትሮ ፖሊታን የፖሊስ መምሪያ (MPD)፣ ስለ ዜግነትዎ ምንነትም ሆነ ወይንም ስለ ነዋሪነትዎ ሁኔታ አይጠይቁዎትም።** የሜትሮ ፖሊታን የፓሊስ መምሪያ ፖሊሶች፣ አንድ ሰው የኢሚግሬሽን ህጎችን ተላለፏል ወይንም አልተላለፈም በሚል መነሻ ሀሳብ የዜግነትን ወይንም የነዋሪነትን ደረጃ ለመወስን እንዳይጠይቁ ፍጹም የሚከለክል ለረጅም ጊዜ የቆየ ፖሊሲ ወይንም ደንብ አለው። ይህም ማለት ወደ ሜትሮ ፖሊታን የፖሊስ መምሪያ ጽሕፈት ቤት (MPD) ፖሊስ በሚያጋጥምዎም ሆነ የተፈጸምን ወንጀል ለማሳወቅ ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ይህም ማለት፣ 911 ለመደወል፣ ወይንም የሜትሮ ፖሊታን ፖሊስ መምሪያ ፖሊስን ለማነጋገርም ሆነ ወይንም ስለተፈጸመ ወንጀል ሪፖርት ለማድረግ አንዳችም ዐይነት ሥጋት ሊያድርብዎ አይገባም። ሆኖም ዲሲ የሜትሮ ፖሊታን መምሪያ (MPD) የፖሊሶችን እርምጃዎች ብቻ የሚቆጣጠር ስለ መሆኑ ልብ ይበሉ። 911 ንም ለመደወል አይስጉ። በመንገድ ላይ ባሉበት ሰዓት፣ የሜትሮ ፖሊታን መምሪያ አርማን (MPD logo) ሲያዩ ልብ ይበሉ።

- **በትምህር ቤትና ከትምህርት ቤት ውጪ፣ ያለምንም ሥጋት ወይንም ፍራቻ በመንግሥት አገልግሎቶች መጠቀምዎን ይቀጥሉ።** የነዋሪነት ደረጃዎ ምንም ይሁን፣ በእርስዎ ላይ ለሚደርስ የወንጀል ተግባር ማመልከት የሚችሉ ሲሆን የሜትሮ ፖሊታን የፖሊስ መምሪያ (MPD) ፖሊሶች እርስዎን ይጠብቁዎታል። ድንገት ቢያምዎትም እንኳን አንቡላንስ ቢጠሩ፣ 911 እና 311 ቢደውሉ፣ ለአረጋውያን ግልጋሎት የሚሰጡ ማዕከላትን ቢጎበኙ፣ በሕዝብ መዋኛ ስፍራዎች ቢጠቀሙ፣ በሰብዌ ማለትም በከተማ የምድር ለም ድር ባቡር ቢጠቀሙ፡ ወይንም በከተማ አውቶቡሶች ቢጓዙ፣ በሆስፒታል አገልግሎቶች ቢጠቀሙ እና ወደ መንግሥት ጽሕፈት ቤቶች ቢዘልቁ፣ የዲስትሪክቱ አስረዳደር ስለ ኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ጉዳይ ሊጠይቁዎት አይችሉም። ይህም የእርስዎ የራስዎ አስተዳደር መንግሥት ጭምር ነው።

- **ዲስትሪክቱ፣ የህጋዊ ነዋሪነት ማስረጃ ወረቀት የሌላቸውን አምልካቾች የመኪና መንጃ ፈቃድ ወረቀት መስጠት አይከለከልም።** ለተውሰኑ ጉዳይ አገልግሎቶች የሚውል መንጃ ፈቃድ (Limited Purpose driver licenses)፣ የማኅበረሰብ ደህንነት፣ የምጣኔ ሀብት አገጎልባችነትን እና የነዋሪነት ወረቀት የሌላቸውን አሜሪካኖች እኩል መብቶቻቸውን ለማራመድ የሚያገለግል ብሄራዊ አርአያነት ያለው ሞዴል ነው። ይህ የዲስትሪክቱ የነዋሪነት እና የምጣኔት ሀብት ዋነኛ አካል የሆነ እጅግ ጠቃሚ መለዮ ነው። ሰዎች የማንነታቸው መገለጫዎች የሆኑ መታወቂያዎች ተከልክለው ከሚቀሩ ይልቅ፣ መንጃ ፈቃድ ቢሰጣቸው፣ የመድን ዋስትና ኢንሹራንስ ቢኖራቸው፣ በጎ፣ መልካም ተግባር እንደሆነ እናምናለን።